# ልዩነትን መሰረት ያደረገ አንድነት  ትርጓሜ ያልገባቸው የሃሳብ መካኖች

**ዮናስ 08/07/13**

ጉዳዩ ጃዋር መሃመድ የተባለው "የፖለቲካ ተንታኝ" በፓልቶክ ያደረገውን ፌዴራሊዝም ተኮር ( ብሄር ተኮር) ቃለ ምልልስ በተመለከተ ሐምሌ 2005 ቁጥር 62 ሎሚ መጽሄት ላይ ያሬድ አይቼህ የተባሉ ፀሃፊና ብስራት ደረሰ የተባሉ ፀሃፊ ያደረጉትን ሙግት በተመለከተ ነው። ያሬድ አይቼህ የተባሉት ፀሃፊ "ውዝግብ በጃዋር መሃመድ ዙሪያ "በሚል አብይ ርዕሥ ጃዋር መሃመድን እና የአማራ ልሂቃንን የተመለከተ ፅሁፍ ያቀረበ ሲሆን ብስራት ታደሰ የተባለው ፀሃፊ ደግሞ ጎረምሳው ጃዋር መሃመድ “ኦሮሞነቴን ካልተቀባላችሁ ከነኢትዮጵያነታችሁ ገደል ግቡ” ይለናል? በሚል ጽሁፍ አስነብቦናል።

በነገራችን ላይ በዚህ የፓልቶክ ውይይት ጃዋር በርከት ያሉና ጽንፍ የወጡ አስተያየቶችን የሰጠ ሲሆን የዚህ ጸሃፊ ትኩረት ግን ልዩነትን መሰረት ስላደረገ አንድነት የጃዋርን ልዩነትን መሰረት ያደረገ አንድነት የሚመስል ግን ደግሞ ጽንፍ የወጣና የአክራሪነት አደጋ በተጫጫናቸው ቃላት የቀረቡትን አስተያየት ተንተርሰው ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁለት ጸሃፊዎች ያደረጉት ሙግት እና በሌላው ጀርባ ላይ ተንጠልጥለው ፌደራላዊ ስርአታችንን ለመሸርሸር የሚሞክሩትን የተመለከተ ነው።

ያሬድ አይቼህ የተባለ ፀሃፊ አማራ ስለመሆናቸው ገልፀው የኦሮሞ አማራ ምሰሶነት ንድፈ ሃሳብን በተመለከተ አቶ ጃዋር መሃመድ “መጀመሪያ ኦሮሞ ነኝ--ኢትዮጵያዊነት ያለፈቃዳችን ተጭኖብን ነው” ማለቱ ለሁሉም ምሶሶዎች ልሂቃን አብሮ መስራት ፍላጎት የመጀመሪያው የአደባባይ ፈተና ነው ሲሉ ገልጸው፣ ሁለቱ ምሶሶዎች አብረው መስራት የሚችሉት ለሁሉም ብሄሮች የሚበቃ ምህዳር ያለው “ኢትዮጵያዊነት” ሲቃኝ ብቻ ነው። ሌላ አቋራጭ መንገድ የለውም በማለት የጃዋርን አስተሳሰብ መቀበል ለአማራ ልሂቃን ግድ ስለመሆኑ ያወሳሉ።

አሃዳዊት ኢትዮጵያ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ያልጠቀመች ኢትዮጵያ የነበረች መሆኑን እና አሁን ብዙሃዊት ኢትዮጵያ መንገዷን የሚተርክልን የአቶ ያሬድ አይቼህ ጽሁፍ ብዙሃዊት ኢትዮጵያ የጃዋር መሃመድ ኢትዮጵያ ስለመሆኗኗ የድሮዋ ኢትዮጵያ ተመልሳ የማትመጣ መሆኑን በመግለጥ የአሃዳዊ ስርዓት ናፋቂዎች እርማቸውን ያወጡ ዘንድ ያሳስባል።

በአማራነት እና በኢትዮጵያዊነት መካከል ከጃዋር መሃመድ አስተያየት ባሻገርም ብዙ ጊዜ ውዝግብ መኖሩን ለምናውቀው አንባቢያን "እኛ አማራዎች ኢትዮጵያዊነትን እና አማራነትን ለይተን ማየት ተስኖናል" የሚለው ፀሃፊ በተለይ አሮጌው ትውልድ በፍፁም ኢትዮጵያዊነትን ከአማራነት አማራነትን ከኢትዮጵያዊነት ለያይቶ ማየት የማይችል የአስተሳሰብ መካኖች በብዛት አሉባት፤ እኛ አማራዎች አንድነት ስንል አንድ አይነትነት ማለታችን መሆኑ ተነቅቶብናል። በማለትም ይተርክልናል። አንድ አይነትነት በግዴታ የሚጫን ማንነት ነው። በሰፊው ኢትዮጵያዊነት ግን ብዙ አይነትነትን የሚያስተናግዱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ ማንነቶች ተንሰራፍተዋል። ስለሆነም ይሄን ማድረግ ያቃታቸው ወይም የጃዋር ንግግር ያልተዋጠላቸው የአማራ ልሂቃን በተለይ በቀድሞው የአሃዳዊ ስርዓት ነፍስ ያወቁቱ ከትግሉ ጡረታ እንዲወጡ የሚመክረው የአቶ ያሬድ ትርክት እንዲህ አይነቶቹ ከትግሉ ጡረታ መውጣት ያለባቸው ለሁለቱ ምሰሶዎች አብሮ መስራት ዋና እንቅፋትና መርዝ በመሆናቸው፣ መርዝነታቸውም ለኢትዮጵያዊነት መስፋፋት መዳበርና እመርታ እንቅፋት በመሆናቸው መሆኑን በማውሳት ትርክቱን ያበቃል፡፡

ታዲያ ይህንና መሰል የጃዋር መሃመድ አስተሳሰብ ደጋፊ የሆኑ ግለሰቦች አስተያየት ወይም ደግሞ ልዩነትን ላስቀደመ አንድነት የሚተጉትንና መስዋእትነትን ከፍለው ብዙህነትን የምታስተናግድ ኢትዮጵያን መመስረት የቻሉ እና በዚህም አስተሳሰብ ውስጥ ለበለፀገች ኢትዮጵያ የሚለፉቱ ሁሉ ያበሳጪቸው አቶ ብሥራት ታደሰ በያሬድ አይቼህ አቀባባይነት ልዩነትን ላስቀደመ አንድነት የተሰለፉ ሃይሎችን ሁሉ ሾላ በድፍን ይቀጠቅጡታል።

የዚህ ፀሃፊም የትኩረት አቅጣጫ የአቶ ብስራት ታደሰ ሾላ በድፍን የሆነ ሙግትና የአስተሳሰባቸውን መካንነት በማስረጃ አስደግፎ ማሳየት ነው።

የአቶ ብስራትን የሃሳብ መካንነት ከሚያመላክቱ ጉዳዮች ውስጥ የመጀመሪያ የሚሆነው ነጥብ ያሬድ አይቼህን "አማራ አይደለም" ሲሉ የዜግነት ካርድ ሰጪና ነሺ ለመሆን መሞከራቸው ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ደግሞ ወይም አማራ የሆነ ሰው እንደያሬድ ስለ አማራነት እንዲህ ሊጽፍ አይችልም ማለታቸው እንደሆነ በመረዳት ሁሉም አማራ ስለአሃዳዊ ስርዓት ያልማል፤ በአንዲት ኢትዮጵያ ስም ምሎ በአንድ ባንዲራ ስም ተገዝቶ በአማርኛ ይፈርማል ብለው ማሰባቸውም ሌላው ስህተትና ደመነፍሳዊነት ነው።

አቶ ብሥራትን ከከነከናቸውና ለመከነ የሃሳብ ውርወራ ያነሳሳቸው ደግሞ "ጃዋር መሃመድ ኦሮሞነቴን ካልተቀበላችሁ ከነኢትዮጵያችሁ ገደል ግቡ" ማለቱ እንደሆነ ዘለፋዊና ድኩማናዊ ትርክታቸው ያሳብቃል። በሌላ በኩል ደግሞ ያሬድ አይቼህን አማራ እንዳልሆነ ላሰመሩበት ሃሳባቸው ፀሃፊው ያቀረቡት ምክንያት ውሎና አዳራቸው ከንባብ ጋር በመሆኑ በዚህም የተነሳ የብእር ስሞችን ለይተው ማወቃቸውን ነው።

ይህ አሰተሳሰባቸው ደግሞ ግዙፉና የመከነ ሃሳብ ጥግ ነው። ለምን ቢሉ ውሎና አዳሩ ከንባብ ጋር የሆነ ሰው መጀመሪያ ነገር ሙግቱ የሃሳብ እንጂ የግለሰብ ሊሆን እንደማይችል የታወቀ በመሆኑ። ሲቀጥልም ውሎና አዳሩ ከንባብ ጋር የሆነ ሰው "ኦሮሞነቴን ካልተቀባለችሁ ከነኢትዮጵያችሁ ገደል ግቡ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ መገንዘብ ስለማይከብደው ነው።

የአቶ አስራትን ከንባብ ጋር ውሎ አዳር ቀርቶ ንክኪም የሌላቸው ስለመሆናቸው የሚያሳዩ ዋቢዎችን ወደኋላ የምመለስበት ሆኖ የጃዋር "ኦሮሞነቴን ካልተቀበላችሁ ከነኢትዮጵያችሁ ገደል ግቡ" ትርጉም ሳይገባቸው ያቀረቡት ትርክት የፀረ ዴሞክራሲያዊ ዋነኛ መፈክር የሆነው የትምክህት አስተሳሰብ ጥግ ጥሩ ማሳያ ነው።

ትምክህተኝነት የአማራ ጥገኛ ባለሀብቶችንና ጥገኛ ምሁራንን ይዞ ካለፉት ስርዓቶች የተረፉትን፤ እነዚያ ስርዓቶች በመገርሰሳቸው ጥቅማቸው የተነካባቸውንና ቁርሾ የያዙ ወገኖቹን አሰልፎ በአግባቡ የተደራጀ ሃይል መሆኑን ለማወቅ ውሎና አዳርን ከንባብ ጋር ማድረግን አይጠይቅም። ይህ ሃይል እንደ ቀድሞ ገዢ መደቦች ሁሉ የአማራውን ህዝብ በትምክህተኝነት በማደናገር መጠቀሚያ ለማድረግ የሚፈልግ ሃይል መሆኑንም ሳናነብ አውቀናል። በዚህ ተልኮአቸውም የአማራውን ህዝብ በሁለት ከፍሎ ለማንቀሳቀስ

ስለመሞከሩ ቀደም ብለን ብንረዳም የአቶ ብስራት ፅሁፍ ደግሞ የበለጠ መረዳታችንን ግልጽ አድርጓል።

ከአማራ ክልል ውጪ በነፍጠኞች በተቆረቆሩ ከተሞች ውስጥ የሚኖረውን የአማራ ህዝብ የአካባቢውን ህዝብ በመናቅ፣ የአካባቢው ሰዎች ባለስልጣናት በመሆናቸው፤ የአካባቢው ቋንቋና ባህል በመከበሩ ኢትዮጵያዊነት እንደተራከሰ አድርጎ በማቅረብ የሚነዛው ነው። ነገር ግን የበላይነት ስሜትን በመቀስቀስ የሚሰራው ስራ ትምክህተኞች ከስልጣን በታገዱበትና የህዝቦች እኩልነት በተረጋገጠበት ሁኔታ ረጅም ርቀት ለመውሰድ የማይችል በመሆኑ ዋነኛው ፕሮፓጋንዳ ይህ አይደለም።

ዋነኛው ፕሮፓጋንዳ የአማራ ህዝብ የበላይ መሆን አለበት የሚለው ሳይሆን የአማራ ህዝብ እየተጠቃ ነው። ኢትዮጵያዊነት እየተራከሰ ነው የሚለው የአቶ ብስራት አይነቱ ጽሁፍ ነው። የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ከመረጋገጡ ጋር ተያይዞ ወይም ልዩነትን ያስቀደመው አንድነት የፈጠረው እራስን በራስ የማስተዳደር ቋንቋንና  ባህልን ማሳደግና በቋንቋ መጠቀምን እውን ካደረገው ፌዴራላዊ ስርዓቱ ጋር ተያይዞ በእነዚህ ከተሞች የሰፈረው የጥገኛ የነበረው የፖለቲካ የበላይነት በመገፈፉ የሁሉም ብሔር ብሄረሰብ ተወላጆች ልክ እንደ ጃዋር በብሄራቸው መኩራት ሲጀምሩ መላው አማራ ጥቅሙ እንደተነካበት ተደርጎ የሚቀሰቀሰው ዘመቻ ጊዜ ያለፈበትና የተበላ ዕቁብ ነው።

እነ አቶ ብስራት በተለይ በእኩልነት ላይ የተመሰረተው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ስር ካለመስደዱ ጋር ተያይዞ የሚሰራቸው ጉድለቶች መላውን ህዝብ የሚጎዱ ሆነው ሳለ በተለይ አማራውን ለማጥቃት የተሰነዘሩ አድርገው ያራግቧቸዋል። የነፍጠኛው ስርዓትና ቅሪቶቹ በተጋለጡና በተወገዙ መጠን አማራና ነፍጠኛ አንድና ያው ይመስል አማራው እየተወገዘ ነው ብለው ይቀሰቅሳሉ። ይህንን የአማራ ተጠቃ ቅስቀሳ በኢትዮጵያ ተዋረደች ተዳከመች ሙዚቃ አጅቦ በማቅረብም ከራሱ ጠባብ አጀንዳ አልፎ አገሪቱን በሙሉ የሚሸፍን ራዕይ ያለው ለማስመሰል ይሞክራሉ።

በአማራ ክልል ያለውን ህዝብ በተመለከተ በአንድ በኩል ከክልሉ ውጪ ያሉ  አማሮች እየተወገዙ፤ እየተበደሉ ነው፣  ነፍጠኛው ሲወገዝ ፌዴራላዊ ስርዓቱ በተግባር ሲረጋገጥና ውጤታማ ሲሆን፣ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብታቸውን በተግባር ማረጋገጥና

በተግባር ማሳየት ሲጀምሩ፤ ውክልናቸውን ተጠቅመው በፌዴራል ደረጃም ሆነ በክልሎቻቸው ማስተዳደር ሲጀምሩ የአማራ ህዝብ ቦታ እያጣህና እየተወገዝክ ነው ብሎ ሲቀሰቅስ በሌላ በኩል ደግሞ በክልሉ የሚከናወኑ ስራዎች ላይ የሚታየውን የታዳጊ ዴሞክራሲ ጉድለት ሁሉ የአማራወን ህዝብ ለማጥቃት ሆን ተብሎ የተደረገ አድርጎ ያቀርበዋል።የአማራው ህዝብ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ በቋንቋው እንዲማር በመደረጉ ይህ አሰራር ለምሳሌ በትግራይና በኦሮሚያ ተገባራዊ መሆኑን በመሸፈን የአቶ ብስራት ወዳጆች የአማራውን ህዝብ ለይቶ ለማጥፋት የተደረገ አድርገው ያቀርቡታል፤ በአሰራር ድክመትና ግብር ለመክፈል ካለመፈለግ ጥገኝነት በሚመነጭ አኳኋን የተማረረውን ነጋዴ በአማራው ላይ እንደተዘመተ አድርገው አቶ ብስራትና የሃሳብ መካኖች ይቀሰቅሳሉ። አርሶ አደሩንም የማዳበሪያ ዋጋ ጨመረ ግብር በዛ፣ እኛ ስልጣን ከያዝን ይህ ሁሉ ይበቃል ብለው ይደሰኩሩታል፡ በአጠቃላይ የታዳጊ ዴሞክራሲው ድክመቶችንና በህዝቡ ውስጥ ያሉ የጥገኝነት አመለካከቶች በአማራ ህዝብ ላይ የተካሄደ ዘመቻ በማስመሰል በኢትዮጵያ ተዋረደች ተዳከመች ሙዚቃ በማጀብ የበላይነት ስሜትን በማርገብገብ ቀላል ያልሆነ ቁጥር ያለው ትምክህተኞችንም ፈጥረዋል፤ አቶ ብስራትም በቅርብ ጊዜ ከተፈጠሩቱ የትምክህተኛው ወሉዶች አንዱ ናቸው።

ስለሆነም ይህንና ከላይ የተጠቀሰውን በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነት መሰረት ላደረገች ኢትዮጵያ መገዛት ለተሳነው ትምክህተኛ ቡድን ልቅም አድርጎ ጨዋታውን የነገረው ጃዋር የዚህኑም አመለካከት ተገቢነት ያብራራውን ያሬድ አቶ ብስራት እንኳንስ አማራ ኢትዮጵያዊ ቀርቶ "ሰው አይደለም" ሲሉ ይዘባበታሉ የትምክህት ጥግ ይሏል ይህ ነው።

ማረጋገጫቸው ደግሞ "አማራ ነኝ ያለ አማራን አይሰድብም" የሚል የልጅ አመክንዮ ነው። በመሰረቱ አቶ ያሬድ አይቸህ ልዩነተን የማታስተናግድ ብዙህነትን የማታስተናግድ ኢትዮጵያ ዳግም ትመለሳለች ብላችሁ አታስቡ፤ ላትመለስ ተቀብራለችና እርማችሁን አውጡ አለ እንጂ ከቶወንም አልተሳደበም፤ ስድብ የባለጌ ቢሆንም አማራ አማራን አይሰድብም ብሎ መደምደሙ ደግሞ የዋህነትና የትምክህቱ ጥግ መንተክተክን የሚያረገግጥ ነው።

አቶ ብስራት በፖለቲካው መስክ የመከነ አስተሳሰብ ያላቸው መሆኑን በዚሁ ፅሁፋቸው ካሰፈሩትና ከዋናው ሃሳብ ጋር ባልተያያዘ የጠቀሱት ነጥብ ጥሩ ማሳያ ይሆነናል ጉዳዩ ሃይሌገብረስላሴን የተመለከተ ነው። ሃይሌ በርግጥም ስፖርተኛ እንጂ ፖለቲከኛ

አለመሆኑን እራሱ ስለራሱ ከሰጠው  ቃል ማግኘት የሚቻል ይመስለኛል ።ችግሩ ግን አቶ ብስራትም ሃይሌ በከፈተው የስህተት በር ዘው ብለው መግባታቸው እነጂ ። ሃይሌ በምርጫ 2007 ለፓርላማ መወዳደር እፈልጋለሁ አለና ፍላጎቱም ፕሬዚዳንት ለመሆን መሆኑን ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃኖች የተመለከቱ መረጃዎች መረዳት ተችሏል። ይህ ነው እንግዲህን የሃይሌ ስህተትና የአቶ ብስራት ውሎና አዳር ንባብ ሳይሆን ወሬ ነው ያልኩበት ምክንያት። ፕሬዚዳንት ለመሆን ፓርላማ መግባት የግድ ነው የሚል አንቀጽ የቱ ጋር ነው በህገ መንግስቱ የሰፈረው? የሚል ጥያቄ ለአቶ ብስራት ባነሳ ውሎና አዳራቸው ንባብ ሳይሆን ወሬ መሆኑን በሚገባ ይገነዘቡታል ብዬ አስባለሁ።

በርግጥ በጃዋር መሃመድ ላይ የተሰጡ ሌሎች ትችቶችን ስንመለከትም ተመሳሳይ የመከኑ ሃሳቦችን ማግኘት እንችላለን። ለምሳሌ በፍትህ ጋዜጣ በልእልና ጋዜጣና በአዲስ ታይምስ መጽሄት ላይ የምናውቀው ሃይለ መስቀል በሸዋምየለህ የተባለ ጸሃፊ ጃዋርን ታዋቂው የፖለቲካ ተንታኝና የመሳሰሉትን በማለት ሲያንቆለጳጵሰው ነው።

አሁን ደግሞ ጃዋር "ኦሮሞነቴን ካልተቀበላችሁ ...."ባለ ጊዜ ሃይለመስቀል አላበው መሰለኝ በአዲሲቱና "ፋክት" በተሰኘች መጽሄታቸው ጃዋርን "ጎረምሳው" ሲል ሰየመው። እንዲህ ነው የትምክህት ፖለቲካ።እንሱ ያሉትን እስካልተቀበልን ድረስ ቢያጡ ቢያጡ በእድሜያችንና በጾታችን ለመፈረጅ ይጥራሉ እንጂ ለሃሳብ ቅድሚያ መስጠት አያውቁበትም ፤አይፈልጉምም።